# የመቋጫው መጀመሪያ

## ክፍል ሁለት

### 1. መግቢያ

በክፍል አንድ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ‘መቋጫው’ በሚል ርዕስ አቶ ልደቱ ለህዝብ ያጋሩትን ጽሁፍ የመጀመሪያ ክፍል አስተያየት ከተራ ቁጥር 1-4 የተዘረዘሩት ላይ በማተኮር ለመዳሰስ ተሞክሯል። በድጋሚ ለማስታወስ ያክልም ከስድስቱ አንኳር የተነሱት ነጥቦች በቅደም ተከተል ከታች ባለው ሠንጠረዥ በድጋሚ የተገለጸ ሲሆኑ አንባቢው ለመከታተል ይመቸው ዘንድ የዚህ ክፍል አትኩሮቶች በዋነኝነት በተራ ቁጥር 6 ላይ የሚያጠነጥን ቢሆንም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በተራ ቁጥር 5 ውስጥ የተነሱ ሃሳቦችን መሃል መሃል ላይ እንደአስፈላጊነታቸው የሚታዩ ይሆናል።

| ተቁ | የፀሃፊው አንኳር ርዕሶች | የትንተናው ዓይነት | የዚህ ግብረ-መልስ ፀሃፊ ጥቅል ግምገማ | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራችን የምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ምን ይመስላል? | ነባራዊ ትንተና | በመስማማት የታለፍ ጥሩ ትንተና ነው | ክፍል 1 |
| 2 | በሥልጣን ላይ የሚገኘው የወቅቱ አገዛዝ ማን ነው? የማንስ ነው? | | በመስማማት የታለፍ ጥሩ ትንተና ነው | |
| 3 | ለወቅቱ የፖለቲካ ቀውስ ያበቁን መሰረታዊ ምክንያቶችስ ምን ምን ናቸው? | | ብዙ እስተያየት ተሰጥቶበታል | |
| 4 | በወቅቱ ፖለቲካ የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች ሚናስ ምን ይመስላል? | የሃይል አሰላለፍ ትንተና | ብዙ እስተያየት ተሰጥቶበታል | |
| 5 | አሁን ባለው አገዛዝና ቀደም ባሉትም የሚነሱ/የሚዘወሩ ሀገራዊ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ምን ዓይነት ግንዛቤ ይኑረን ? | የቀድመ-መፍትሄ ቀሪ አንኳር አጀንዳዎች ትንተና | የተወሰነ አስተያየት እንዲሰጥበት የሚጋብዝ ትንተና ነው | ክፍል 2 |
| 6 | የችግራችን አጠቃላይ መፍትሄዎችስ ምን ምን ናቸው? | የመፍትሔ ትንተና | የተወሰነ አስተያየት እንዲሰጥበት የሚጋብዝ ትንተና ነው | |

ከላይ የተዘረዘሩትን የአቶ ልደቱ አያሌው ጽሁፍ በዚህ መልኩ ለመገምገም የተነሳሁበት ዓላማ ሁሉን-ዓቀፍ ውይይት እንዲፈጠር፤ ‘ያገባኛል’ የሚል ሁሉ ያቅሙን እያዋጣ ቢያንስ በተወሰኑ የጋራ ኣላማዎች ላይ እንዲያተኮር ካለኝ ፍላጎት እንጂ ለጉንጭ አልፋ ክርክርና ጸጉር ከሚስነጠቅ አቃቂረኝነት ተነስቼ እንዳይደለ በድጋሚ አስታውሳለሁ። የክፍል ሁለት ግምገማ **‘መቋጫው’** የሚለው የአቶ ልደቱ ጽሁፍ **ተግባራዊ መጀመሪያ** ሊኖረው ስለሚገባ በፅሁፉ የተዘረዘሩትን ምክረ ሃሳቦችንም ሆነ ሌላ አማራጭ መፍትሄዎችን እንዴት ወደመሬት እናውርድ በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ላይ ነው የሚሆነው።

አቶ ልደቱ የመፍትሄ ሃሳባቸውን የአጭር እና ረጅም በማለት ከፈሉት ሲሆን በመቀጠልም የአጭር ጊዜ መፍትሄ ብለው የጠቀሱትን ሃሳብ ይዘት አብራርተው መፍትሄውንም ማን ሊያዋልደው እንደሚችል ከቅደሚያ ግምታቸው ጋር አስፍረዋል። ዙርያው-ገደል ከሆነበት አደገኛ ሁኔታ መለስ ካልን በኃዋላም በዘላቂነት የሃገሪቱን ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት ጠቃሚ ናቸው ያሏቸውን ሶስት ነጥቦች አስቀምጠዋል። በቀጣይ ለምናደርገው የሃሳብ ማብላላት እንዲረዳ ከዚህ በታች ባለው መልኩ በሠንጠረዥ የፅሁፋቸውን ይዘት በማሳጠር አስቀምጫለሁ።

| | የመፍትሄ ሃሳቦች | |
|---|---|---|
| | **የአጭር ጊዜ** | **የረጅም ጊዜ** |
| | 1. ተኩስ ማቆም<br>2. የቅድመ ሽግግር አገራዊ የውይይትና ድርድር ሂደት(አውድሂ) ማካሄድ እና<br>3. የሽግግር መንግሥት ማቋቋም | 1. ፖለቲካን ከትምህርት እና እርሻ-ጠል ግለሰቦች ማጽዳት<br>2. የፅንፈኝነትና የጦረኝነት ልማዳችን በሰላማዊ የፖለቲካ ባሕል መተካት<br>3. የብሔርተኝነት ፖለቲካ የአገራችን መዋቅራዊ ገዥ መሆኑን ማስወገድ |
| ተዋንያን በቅደም ተከተል | 1. አብይ አህመድ<br>2. ብልጽግና ፓርቲ<br>3. ተቃዋሚው ፓርቲና እና ህዝቡ | [የረጅም ጊዜ ዕቅድ እና ጥቅል ከመሆኑ አኳያ የመፍተሄ ሃሳቦቹ ፈጻሚያን ባይጠቀሱ አይገርምም።] |

## 2. የመፍተሄ ሃሳቦቹ በጊዜ እና ፈጻሚያን አከፋፈል

እንደ ጥሩ ነገር ከአቶ ልደቱ ልንወስደው የሚገባው ትምህርት መፍተሄዎች ከጊዜ አንጻር ለቃኙ እንደሚገባ ማመልከታቸውን ነው። ምናልባትም በክፍል አንድ ላይ በአፅንኦት 'ምን ዓይነት ትንታና ነው በዚህ ጊዜ የሚያስፈልገን?' ብለን የጠየቅንበትን መነሻ በሚደግፍ መልኩ 'ከገደሉ አፋፍ' ወደኃላ የምንመለስበትን መንገድ በመፍትሔ ደረጃ በዚህኛው የጽሁፋቸው ክፍል ላይ ተጠቁሟል። ተከሱን አቁመን(1)፤ የልሂቃን ድርድር በማድረግ (2) የሽግግር መንግስት መመስረቻ የቃልኪዳን ሰነድ ማዘጋጀት (3) የተባሉትን ሂደቶች በጥቅሉ ካየናቸው እና ከተሳካ ትልቅ እርምጃ ነው። እዚህ ጋር ግን የተወሰኑ ጥያቄዎችን እያነሳን ጉዳዩን ስናፍታታው በልጅነታችን ከሰማነው እያደነች ካስቸገረቻችው ድመት ማምለጫ ዘዴ ለማፈላለግ አይጦች ያደረጉትን ስብሰባ ያስታውሰናል። በስብሰባው ላይ የቀረበው የመጨረሻ ግሩም ሃሳብ የድመቷን እንቅስቃሴ የሚያሰብቅ ቃጭል አንገቷ ላይ ማሰር ሲሆን የታሪኩ መደምደሚያ ደግሞ 'ማን ነው ቃጭሉን አንገቷ ላይ የሚያስረው?' የሚል የአንድ ጠና ያለ አይጥ ጥያቄ ነው። ባደኩበት ማህበረሰብ የዚህ ታሪክ ሞራላዊ ትምህርቱ 'ምን ጥሩ ቢሆን የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገር!' ይሉት ፈሊጥ አለው። በሌሎች ሰዎች አተያይ ሲተረጎም ደግሞ 'ድመቷን መቀጨል' ከባድም አደገኛም ለማሳካትም የሚቻል የማይመስል ነገር ተደርጎ ቢታሰብም ከፍተኛ መቻቻልን፣ ሆደ-ሰፊነትን፣ ፅናትን፣ ብልሃትን፣ ትብብርን፣ ድፍረትን ከያዝን ግን የማይቻል ነገር አለመሆኑን ነው።

### 2.1.ድመቷን መቀጨል የማይቻል የሚመስለው ለምንድነው?

በስልጣን ላይ ያሉት መሪ በብዙ መልኩ መሪነታቸውን አይነኬ ለማድረግ ተግተው የሰሩ ሰው ናቸው። በኢህአዲግ የፓርቲ ባህል ውስጥ ያለው የቡድን አመራር ዘይቤን በጊዜ ከስሩ ቆርጠው ስለጣሉት 'እንዲህ አጥፍተሃል እዚህ ጋር ተሳስተሃል' የሚል የሌለባቸው ሁሉን ቻይም ሁሉን አዋቂም ሆነው በዙፋናቸው ነው ያሉት። ለቅርቦቻቸው በማይመለስ ጭካኔ ተቀናቃኝ የሚመስሏቸውን በሚያሳድድ የለየለት አምባገነንነት ላይ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ደርሰዋል። እስከዛሬ ከነበሩት መሪዎች በሚለይ ሁኔታ 'በገንዘብ የማይገዛ ስብዕና የለም' በሚል ፍልስፍና በእጃቸው ላይ ያለውን የሀገር ሃብት ያለስስት ድጋፍ ለመግዛት ሲሉ ከመበተን ወደኃላ የማይሉ ሰው ናቸው። በስልጣን ላይ መቆየታቸው በራሱ የመጨረሻ ግብ እንደሆነ ያክል ዙፋናቸውን ለመጠበቅ የሀገሪቱን ሙሉ በጀት ለጦርነት እንደሚያውሉ በግልጽ ሳይደብቁ የሚናገሩ መሪ ናቸው። የጦር ሠራዊቱን ከፍተኛ መኮንኖች በመሬት፤ በገንዘብ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች


የሚደልል፣ከጎረቤት ሃገራት ጋር የራሱ ህዝብ እና ግዛት ላይ ሸርክና የሚዋዋሉ ገራሚ መሪ ናቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ። አቶ ልደቱ የዘረዘሯቸውን ገላጮች ጨምሩበትና አንቀጹን እንጠቅልለው። የገጠመን ድመት ለመቀጨል ከባድ ነው።

ከላይ በተጠቀሱትና ሌሎች ተጨማሪም ምክንያቶች ከእኚ መሪም ሆነ የመመለክ ያክል ከገኑበት ፓርቲያቸው የአጭር ጊዜ መፍተሄ አዋላጅነትን መጠበቅ የዋህነት ነውና በምንም ለጋስነት ባየው የ10 መቶኛ ዕድል ያለው አይመስለኛም። አንዳንድ አፈንጋጭ አመራር አይኖርም ባይባልም በየተራ ዘብጥያ ከመውረድ በቀር ጠሚውን የሚያወርዳቸውን ማዕበል ሊፈጥር የሚችል ስብዕናም፣ አስቻይ የፓርቲ መዋቅርም የለም። ምንም በማያጠራጥር ሁኔታ የብልጽግና ጭፍራ ጠ/ሚ አብይን ያለፍርሃት የሚከዳቸው ስልጣን የለቀቁ እለት ወይም ፓርቲው በፈረሰ ማግስት ነው። በዚህም ምክንያት ከመቶኛ ይሰላ ከተባለ የሁለቱም የአጭር ጊዜ መፍትሄ የማምጣት ዕድል ለዜሮ የቀረበ፣እንደኔ ዓይነቱ በተአምር ለማያምን ግለሰብ ሲያሰላው ደሞ የተደላደለ ዜሮ ነው።

## 2.2. አሁንስ ተስፋዬ ማነው?

አቶ ልደቱ ከዘረዘሩዋቸው ሶስት መፍተሄ አምጪ ሊሆኑ ይችላሉ ከተባሉት መሃል የመጨረሻውና በአንፃራዊነት ሚዛን ደፍቶ የተገኘው 'የተቃዋሚው ጎራ እና ህዝቡ' የሚለው ነው። እንደፀሃፊው ግምት መፍትሄው እውን የመሆኑ ሁኔታ ሲሰላም ከ25% እንደማይበልጥ ይገልፃሉ። በአቶ ልደቱ በኩል  በዚህ መፍትሄ ሥር የተዘርዘረው ከማጠሩ አኳያ ብዙ ጥያቄ ያጫራል። ነፍጥ አንግበው የሚፋለሙቱ ከ'ተቃዋሚው እና ህዝቡ' በሚለው ስር ይጠቃለላሉ? ልደቱ የሰላማዊ ትግል አራማጅ ናቸው ብንልም በጊዜ ሂደት የሃይል ሚዛኑ ተቀይሮ አንድ ሁለት ብለን የዘረዝረናቸውን መፍተሄዎች በአስገዳጅነት ጠረጴዛ ላይ የሚያመጡት ነፍጥ ካነገቡት ወገን ሊሆን ስለሚችሉ ይህን መሰል ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን። በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ያለዕረፍት እየተዋጋ ያለው ጦር ሰራዊትስ አገዛዙን በቃህ ሊለው ይችላል? የመሆን ዕድሉ እንደኔ እንደኔ ዜሮ ስላለሆነ ከትንታኔ ዕይታ ውስጥ ማውጣቱ ትክክል አይመስለኝም። ለምን ቢባል የህዝቦች የነፃነት እና ወደ መልካም አስተዳደር የሚደረግን ረጅም ጉዞ ስልጣን የያዘን አካል መታገል ብቻ ሳይሆን ነገ ቀጥተኛ ስልጣን ሊይዝ የሚችል አካልንም መግራት ስለሚያጠቃልል ነው።

ከላይ ከዘረዘርናቸው ቀጥተኛ የስልጣን ኮሪደር ተናጣቂዎች (ምድብ 1) ውጪ ያሉ አካላት መፍትሄውን በማዋለድ ረገድ ምን ሚና ሊኖራቸው ይችላል ብሎ እዚህ ጋ መጠየቁ አግባብ ነው፡፡ በምሁርነት ልቀው በሃብት ገዝፈው በማህበራዊ ጥሪታቸው አንቱ የተባሉቱስ ምን በጎ አስተዋፅዖ ሊኖራቸው ይችላል ብለን መጠየቅ ያለብን ወቅት አሁን ነው፡፡




በተለይ በምድብ 1 ላይ ያሉት አካላት እንደጊዜው የሚቀያየር ቀጥታ ሊመነዝር የሚችል የመከወን ጉልበት ስላላቸው በማንኛውም ጊዜ ለብዙሃኑ ጥቅም የሚገዙ ለማድረግ ጠንከር ያለ አደረጃጀት ቀድሞውኑ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ምንአልባትም አቶ ልደቱ ከተኩስ አቁም በኃላ ይከተላል ያሉትን የውይይትና ድርድር ሂደት በ'ተቃዋሚ ሃይሎች' መሃከል ከሚደረግ ይልቅ በሊሂቃንን መካካል ቢደረግ በሚከተሉት ምክንያቶች ጥሩ ይሆናል፡፡

- ለሀገሪቱ ፈርጀ ብዙ ችግሮችን በእውቀት ላይ ተመስርቶ መፍተሄ ሊያበጅ የሚችለው ይህ ስብስብ በተለያዩ ምክንያቶች ራሱን እንደ ንቁ የፖለቲካ ተዋናይ ስለማያይ በ'ተቃዋሚ ጎራ' በሚለው ቅንፍ ውስጥ አናገኘውም፡፡ ለፖለቲካ የሚያሳየው ባይተዋርነት መነሻ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩት ቢችሉም፤በቅርብ ጊዜ ዓይነ-ጥላው ተገፎ ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ ያደርጋል ተብሎ ስለማይጠበቅ በመረጠው አውድ አበርክትዎን መጠቀም ስላለብን

- የልሂቃን ውይይትና ህብረት መሰረቱ ሰፊ ስለሆነና የቀጥተኛ ስልጣን ተናጣቂ ስላልሆነ የተከፋፋለውን የህዝብ ክፍል ለማሰባሰብ ከ'ተቃወሚው ጎራ' ይልቅ ተዓማኒነት ሊጣልበት ስለሚችል፡፡
- እስካሁን ባለው የሶስትዮሽ መስተጋብር ሊሂቃን እንደ ፋና-ወጊ የህዝብ ልጆች ስልጣንን ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ከመግራት አኳያ ያላቸውን የማይተካ ሚና ሊጀምሩ የሚችሉበት ወርቃማ አጋጣሚም ዛሬ ስለሆነ
- አሁን ያለንበት ወቅት የሚፈልገው ሁነኛ የትግል ምዕራፍ መሠረታዊ ስምምነት መፍጠር የሚያስፈልግበት ስለሆነ ከየትኛውም ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊ አካል ይልቅ በእርስበእርስ ንትርክ ጊዜ የማያጠፋ እና ያነሰ ዋልታዊነት (polarization) ስለሚያሳይ

አቶ ልደቱ 'ሕዝቡን በየደረጃው ሊወክሉ የሚችሉ ሲቪል ተቋማትና ተፅዕኖ ፈጣሪ ወገኖች' ብለው የገለጹት በአብዛኛው በዚህ ጽሁፍ 'ሊሂቃን' ተብለው በምድብ 2 ከተዘረዘሩት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም በእኔ አተያይ የ'ተቃውሚው ጎራ' ታናሽ ተባባሪ(junior parthner) ሆነው ሳይሆን ለብቻቸው እንደመፍትሄው አስጀማሪዎች ቢገለጹ መልካም ነው፡፡

## 2.3. የአጭር ጊዜ መፍተሔው ምን ሳንካ ሊገጥመው ይችላል?

በአጭር ጊዜ መፍትሔነት የተቀመጡት ጉዳዮች ከዚህ ቀደሞም እንዳልኩት በጥቅሉ የሚያግባቡ ናቸው፡፡ የትጥቅ ትግልን ግዴታ የማያደርግ ነባራዊ ሁኔታ ተፈጥሮ የጠብምንጃ ላንቃ ፅጥ ቢል መልካም ነው፡፡ ወደ ዲሞክራሲ ለመመለስ የሚደረግውን ጥረት የሚያግዝ የሽግግር ጊዜም፤ ከሽግግሩ ጊዜ በፊትም የውይይትና የደርድር ሂደት ማስፈለጉ አያከራክርም፡፡ አቶ ልደቱ እንዳሉት የተዘረዘሩት የአጭር ጊዜ እርምጃዎች በስልጣን ላይ ያለው ሃይል (ጠሚውና ብልጽግና) አምኖባቸው በቁርጠኝነት ወደ መፈጸም ካልተገባ (እድሉ ለዜሮ የቀረበ መሆኑንም ሳንዘነጋ) ሌላ ተለዋጫ እቅድ(Plan B) ማሰብ ግድ ነው፡፡ እዚህ ጋ ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ ተለዋጭ እቅዳችን አንድ ጦረኛ መሆኑን ደጋግሞ ያሳየንን መንግስት ካለፍላጎቱ የተኩስ አቁም እንዲፈርም እንዴት ሊያደርገው ይችላል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተኩስ ማቆም የአጭር ጊዜው መፍተሄ የመጀመሪያ ቅድመ-ሁኔታ ተደርጎ የተቀመጠ ስለሚመስል፤ ይህም በሚከተሉት ምክንቶች አዋጭ ላይሆን ይችላል ብዬ አምናለሁ፡፡

**አንደኛ**: ተፋላሚዎችን ከራሳቸው ፍላጎት ውጪ እዚህ ግዴታ ውስጥ ማስገባት ማንም የሚቻለው ስላይደለ እና ለአጠቃላዩ ሂደት ቅድመ-ሁኔታ በመሆን የመፍትሄውን ፍጥነት እንዳይጎትተው

**ሁለተኛ**: ተፋላሚዎችን እየገሩ የሠላም መንገድን እንዲከተሉ ለመጫን ወይም ጫና ለማድረግ የሚችሉ ተዋናያንን (የፕሪቶርያው ሶስተኛ ወገን አደራዳሪዎችን የመሰሉ) ለመድረስ በውይይቱ የሊሂቃንን ሁሉን-ዓቀፍ ቅድመ-ተግባቦት መገንባት፤መታመን አስፈላጊ ሰለሆነ

**ሶስተኛ**: ልሂቁ ተሰብስቦ የሚነጋገረው ነገር ጠሚው እንደሚሉት የሚንስትር ቦታዎችን ለመከፋፈል ሳይሆን የመግባባት መደላድል ለመፍጠር መሆኑንና ልዩነትን ተነጋግሮ ማጥበብ መቻሉን ለሃይል ኮሪደር ተናጣቂዎች የማሳየት ሞራላዊ ግዴታ ስላለበት

**አራተኛ** : ሂደቱ ጊዜ የሚፈጅ አሰልቺ አንዳንዴም እልህ አስጨራሽ ሊሆን ሰለሚችል ቅድሚያ ተሰጥቶት በቶሎ መጀመሩ የተሻለ ሰለሚሆን


እዚህ ላይ በደማቁ ሊሰመርበት የሚገባው ቁም ነገር፤ የሊህቃን ውይይት ከቀጥተኛ የሃይል መናጠቅ ውስጥ ለመግባት ፍላጎት በሌላቸው ፍቃደኛ የአደባባይ ምሁራን፤ የህብረተሰብ አንቂዎች፤ ያልጎደፈ ማህበራዊ ምንዳ (social capital) ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች የሚካፈሉበት መድረክ ነው። እንዲስማሙባቸው የሚጠበቀው በጣም መሰረታዊ የሆኑ አንኳር ጉዳዮች (Bare minimums) ብቻ ናቸው። ለሁሉም ፍቃደኛ ተሳታፊዎች ሀገር የማዳን ግዴታቸውን ሳያሳኩ ከንግግሩ የሚወጡትን በሚከተለው የስንብት ቃል ሃላፊነታቸውን እንደተዉ የሚቆጠርብትን መንፈስ መፍጠር አስፈላጊ ነው።

> **በነጻ መንፈስ እና በበጎ ህሊና፤በመስጠትም በመቀበልም፤ ብዙዎች ስንሆን ህዝባችንን ለማዳን አንድ መሆን ካልቻልን፤ ከእኛ በሞራል ከፍታ የወረዱ፤በእውቀት እጦት ምክንያትም መሪ መሆን በማይገባቸው ለመመራት በራሳችን ፈርደናል፡፡ ነጻነት ቢያሰፈልገንም ስናገኘው የምንሸከምበት ትከሻ የለንምና ለባርነት ጎንበስ እንላለን እንጂ አናጉረመርምም፡፡**

ነገር ግን የመጨረሻውን ትንሹን የመግባቢያ መሰረት ማስቀመጥ አለመቻል ሊሆን የማይችል ክፉ ዕጣ ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ይህ ንግግር እና ትብብር እንዳይሳካ ሳንካ ሊፈጥሩ የሚችሉት ጉዳዮች ብዙ ናቸው። አንደኛው እና ዋነኛው ሳንካ የ'ሽግግር መንግስት' የሚለው

አገላለጽ ‘ህገመንግስቱ ላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማድረግ የሚያስችል አካሄድ ነው’ ብለው የሚያስቡ ጥቂት የማይባሉ ግራ ዘመም ፖለቲካዊ አተያይ ያላቸው ወገኖች መኖራቸው ነው። ‘ሀገር ሊፈርስ ነው’ በሚል ግርግር በበቂ ስራ ላይ አልዋልም የሚሉትን ህገመንግስትና የፌደራላዊውን መዋቅር ከእናካቴው የሚከልስ ሂደት ውስጥ ሰተት ብለው እንደማይገቡ በአሁኑ ሰዓት እንኳን እየተደረጉ ያሉትን እሰጥ-አገባዎችን መታዘብ በቂ ነው። የውይይቱ ዋና ዓላማ ይህ እንዳልሆነ ማስረዳት ማዶ ለማዶ ሆኖ ከመጨቃጨቅ ያድናልና ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህ የሊሂቃን ህብረት በምሥረታ ሂደቱም ሆነ በሁለት እግሩ ከቆመ በኃላ ከውስጥ ቦርቧሪዎች መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ቦርቧሪዎች ውስጥ ሆነው የለየለት የፖለቲካ ዘውግ(faction) በማራመድ፤ ለይቶላቸውም ስልጣን ላይ ላለው ስብስብ ስልታዊ ድጋፍ  በማደረግ ህብረቱን ሽባ ሊያደርጉት ይችላሉና ሊታሰብበት ይገባል።

ከዚህ በታች የሊሂቃን ውይይት፤እሱንም ተከትሎ ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀውን መሠረታዊ መግበቢያ (The bare minimum manifesto) እና እውን የሚሆነው የሊሂቃን ህብረት የሚያከናውናቸው ስራዎችን በስዕላዊ ከዚህ በታች እንዳለው ተገልፆል።



በተባበረ የሊሒቃን ህብረት ሊተገበሩ ይገባቸዋል ብዬ የማስባቸውን ስራዎች ከዚህ በመቀጠል ምሳሌ በመጥቀስ አስረዳለሁ።

*ሀ. የሃይል ኮሪደር ተናጣቂዎችን መግራት*

*መንግስትም ሆነ ነፍጥ ያነሱ ተቃዋሚዎችን የተኩስ አቁም እንዲያደርጉ ግፊት ማድረግ የሚችለው የዚህ የሊሂቃን ህብረት ስራ ነው። አልያ አቶ ልደቱ እንዳሉት የትግራይን ጦርነትን ያቆመው 'ጦርነቱ ነበር' እንዳሉት ሆኖ ወይም ሃያላኑ እጃቸውን አስገብተው በጫና ከሆነ ብቻ ነው ጠመንጃ ፀጥ የሚለው። ሁለቱ በሌሉበት ሁኔታ ተኩስ ይቁም ብለን ሁለቱንም ብንማፀን የሚሰማን ይጠፋና የማያባራ ግጭት ዕጣ ፈንታችን ይሆናል። አንዳንዴም እንደ ዕድል በሚቀጠርበት ደረጃ ለደርድር ጫናው ክፍ ይልና እንደ ባለፉት ሁለት ያልተሳኩ በኦነስ(OLA) እና ፌደራል መንግስቱ መካከል ድርድር ሲደረግም ሲፋረስም አይተናል። ድርድሩ ላለመሳካቱ የሚወቀስ(ሁለቱም ወይም አንዱ) ማን እንደሆነ በበቂ ጥልቀት የሚመረምር፤ የሚወቅስ እና የዓለም-ዓቀፉን ማህበረሰብ የሚያስረዳ ተዓምኒነት ያለው ኢትዮጵያዊ ስብስብ አላየንም። ብልፅግና የኦነስን መሪዎች በለመደበት ርካሽ መንገድ ለመደለል ሞክሯል? ወይስ ኦነስ በእብሪት እና ስግብግበነት ካቅሙ በላይ ጠይቋል? እውነቱን ወደግራም ሆነ ወደቀኝ ያዘመመ ፖለቲካዊ አተያይ ያልተጫነው ተሰሚ ቡድን ቢናገረው ይደመጣል፤ይጫናል፤ለውጥም ያመጣል። ከዚህ በተረፈ በተበታተነ ሁኔታ ጠቅላይ ሚኒስተሩንና ሌሎች ተባባሪዎቻቸውን ሚዲያ ላይ ከማብጠልጠል ይልቅ ለታሪክም የሚቀር የ'ይበቃል' ቀጥተኛ መልዕክት ማስተላለፍ ይዚህ የሊሂቃን ህብረት ሃላፊነት ነው። ነገ የሚባል ነገር እንዳለ ከመንግስተ እሰከ አማጺ ሃይሎች፤ ከአገዛዙ ቁንጮ እስከ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ድረስ ያሉትን ማስገንዘብ የሚኖርበት አካል ካለ ይህው የሊሂቃን ህብረት ነው።*

**ለ. ህዝቡን ለመጪው ዘመን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ማዘጋጀት**

በዚህ ፅሁፍ ማጠቃለያ ላይ የረጅም ጊዜ መፍትሄ የተባለውን ስንወያይ ሰፋ አድርገን የምንመለስበት ጉዳይ ቢሆንም የሊሂቃን ህብርት ከመመስረቱ ማግስት ጀምሮ በዜጎች መሃል ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲሰፋ በራሱም ምሳሌ በመሆን፤ መማሪያ መድረኮችንም በመፍጠር ትልቁን አስተዋፅዖ ሊወጣ ይገባል። አገዛዙ ከታሰበውም ፈጥኖ መንገዱን ቢለቅ ለቀጣይ ስራ እንቅፋት የሚሆነው ነገር በዲሞክራሲያው ባህል ያልተደራጀ ህዝብ ነው። ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ እንዳይሆን ነገሩ ረጅሙን ጉዞ ከምንጀምርባቸው ቦታዎች አንዱ ይሄ ነው

ብዬ አምናለሁ። የቅድመ እና የድህር አብዮት ቀዳሚ አመታት (1960ዎቹ አጋማሽ እስከ 1970ዎቹ መጀመሪያ) ላይ የነበሩትን የዜጎች ፖለቲካዊ እንቅስቃሴን ትኩሳት በሚያስታውስ የያገባኛል መንፈስ ስለ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ፤ ስለዜጎች መብትና ግዴታዎች፤ስለምርጫ እና የመሳሰሉ ሃሳቦችን የሚያሰርፁ ምሁራዊ ግባአቶችን በማዘጋጀት ማነቃቃት እና ማስተማር ይገባል። ይህ በተለምዶ 'የኢህአፓ ዘመን' የሚባለውን የፖለቲካ ልምምድ ዳግም ቁንጠኛ ለማድረግ የሚያልም የጅል ቀልድ ሊመስል ይችላል። ነገርዬው ጅልም አይደለም፤ቀልድም አይደለም። ነገሩ ድመቷን እንደመቀጨል ከባድ እና የማይቻል የሚመስል ጉዳይ ነው። አቶ ልደቱ ያዋጥል ብለው ለሚከራከሩለት ሰላማዊ ትግል መሰረቱ ሊጣል የሚችለው ምን እንኳን ቀርፋፋ ቢመስልም በዚህ ዓይነቱ በዘመኑ ቴክኖሎጂ የታገዘ የባህል አብዮት ሲቀጣጠል ብቻ ነው።

## ሐ. በተቀናጀ ድምጽ የሀገሪቷን ሁኔታ ለውጪው ዓለም ማስረዳት

ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ አበርክቶት ያላቸው የውጪ ሃይሎች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ያክል አውሮፓ ህብረትን የባለፉት 6 ዓመታት አወንታዊ ሊባል የሚችል የኢፍትአዊነት ሰለባ ለሆኑ ሃገሪቱ ዜጎች ያሳየውን አጋርነት(የእርስ በእርስ ጦርነትን የሰብዓዊ ጥሰቶችንና የምርጫ ሂደትን በተመለከቱ ጉዳዮች) የሚደነቅ ነው። ለዚህ ዓይነቱ ወዳጅ ሀገሪቱ ወደ ተሻለ መንገድ እንድትገባ የሚያግዝ ሃገር በቀል የዜጎች ህብረት እንዳለ የማሳየት የዜግነት ሃላፊነት አለብን። እንደ አሜሪካ ኖረዌይ እና ኬንያ ያሉ ሀገራት ተፋላሚዎችን ለማሸማገል እያደርጉት ያለው አስተዋጽዖ ጉልህ ሆኖ፤በራሳችን ሊሂቃን የተቀረፀ የሁኔታ ትንተና ቢቀርብላቸው ድጋፋቸው የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን እናግዛለን። በትንሹ ድህረ-አብይን እንደ ድቅድቅ ጨለማ (uncharted waters) ሆኖ የሚታውን ነገር ዐይነ-ጥላውን ይገፈዋል። በአጭሩ ሀገሪቱ ላይ መከተል ስላለባቸው ፖሊሲ ሲያጠኑ ከመንግስት ውጪ ሊያማክሩት የሚችል የሚታመን አቻ አደረጃጀት ለመመስረት የዚህ ህብረት ዋነኛ ግብ መሆን አለበት። አምባገነን መሪዎቻችንን በገንዘብም፤በመሣሪያም የሚረዷቸው ሃያላንን የድርጊታቸውን አውድ እንዲያጤኑት ሊነገራቸው ከተፈለገ መልዕክቱ መተላለፍ ያለበት በዚሁ ሊታመን በሚችል የሊሂቃን ህብረት አማካኝነት ነው። ሲጠቀለል የታዬ ዐጽቀስላሴን የውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤትን የሚገዳደር ትይዩ ሚኒስትር (shadow ministery) በብሩህ የዘርፉ ባለሙያዎች ስብስብ መፍጠር ድመቷ አንገት ላይ ቃጭሉን የማሰር ሥራ ዋናው መጀመሪያ ነው።

## 2.4. ተቃዋሚውና ጎራ እና ህዝቡ

የተቃዋሚው ጎራ የምንለው ስብስብ ዲሞክራሲ ብልጭ ድርግም በሚልበት የሀገሪቱ የፖለቲካ መድረክ አማራጭ ለመሆን አነሰም በዛም ሞክሯል። የእድሜውን ያክል ግን ውጤት አሳይቷል ማለት ግን ሀሰት ይሆናል። ከግራ ዘመም እስከ ቀኝ በርዕተ-ዓለም ምርጫ ተዘርግቶ፤ በመንግስት ሴራም በራሱም ድክምት እንደ ዕድር ድንኳን ሲጣል ሲፈርስ የከረመ ስብስብ ነው። በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ትርጉም ያለው ክርክር ከገዢው ፓርቲ ጋር የማድረጉን ያክል፤ ዘቅጦም የአምባገነን መንግስት አጋፋሪ ሆኖም አይተነዋል። ውስጠዊ ዲሞክራሲም ሆነ ተባበሮ የመሥራት መንፈሱ አንድ ሀገር በሚያስፈልጋት ተፎካካሪ አማራጭነት ደረጃ ነው ማለት ውሸት ይሆናል። ከጥቂቶች በ 'ያገባኛል' መንፈስ ከተቀላቀሉት የምሁር ሊሂቃን በቀር አብዛኛው በ'ይገባኛል' ድፍረት ዘው ያሉ ግለሰቦች የሚበዙበት የአረም እርሻ ነው። ራሱን ከስህተቶቹ አርሞ ጥንካሬውን ካላጎለበተ ለይስሙላ ምርጫ (የፊታችንንም ጨምሮ) አዳማቂ ከመሆን የሚያልፍ አይደለም። ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ ብለን እንዳንተወው ደግሞ ካለጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዴት እውን ይሆናል? ላም እሳት ወለደች ሆኖ እንዳይቀጥል ለሀገራዊ ውይይትና ድርድር ላይ ከመቀመጡ በፊት የራሱን ጥልቅ ግምገማና ግለሂስ ማካሄድ ተዓማኒነቱን ለመገንባት ወሳኝ እርምጃ ነው። እንደ አብይ አህመድ ራሱን-መገምገም-የተሳነው (incapable of selfreflection) ሰብስብ አለመሆኑን ማሳየት ይጠበቅበታል።

ስለህዝቡ እና የወል ችግሮቻችን በክፍል አንድ በመጠኑ ስለተባለ የሚጨመር ቀሪ ብዙ ነገር የለም። ነገር ግን 'ህዝቡ' በትግሉ ውስጥ ሊኖረው ስለሚገባ ተሳትፎ ጥቂት ነገሮችን መወያየት ያለብን ይመስለኛል። አንዳንዶቻችን በሁሉም ከተሞች ያለ ህዝብ ግልብጥ ብሎ አደባባይ በመውጣት ተቃውሞውን እሁድ ቢያሰማ ሰኞ መንግስትን መቀየር እንደሚችል እናልማለን። ጠሃሪር አደባባይ ወጥቶ 'ሙባረክ ካልወረዱ ወደቤት አልመለስም' እንዳለው የካይሮ ህዝብ ህዝባችን እንዲሆን እንመኛለን። ምኞት ባይከለከልም ከእንደዚህ ዓይነት የህዝብ ማዕበል በፊት የፖለቲካዊ ጥያቄውን ዓላማ ፍንተው አድርጎ የሚስል ግንባር ቀደም የሊሂቃን ሥራ መስራት ይቀድማል። 10 ሚሊዮኖች በአንድ ድምጽ አደባባይ እንዲወጡ፤በትንሹ 1000 ሊሂቃኖቹ በህብረት ሲቆሙ ማየት ቅድም ሁኔታ ነው። ወደህዝብ አልተኩስም የሚል ወታደር በሌለበት ሀገር፤የመኖር ህልውናው የብሔር ልዩነቱ በጋረደው ሀገር፤ ይህም ከተሳካ እንደ ዕድል የሚቆጠር ነው።

## 2.5.ረጅም ጊዜ መፍተሔውስ ላይ ምን ሊባል ይችላል?

የርጅም ጊዜ መፍትሄው ለየትኛውም ሀገረ-መንግስት በዲሞክራሲያዊ ልምምድ የነቃ እና የተደራጀ ህዝብ መፍጠር ነው። እንዲያ ሲሆን አቶ ልደቱ እንደተመኙት የኢትዮጵያ ፖለቲካ የትምህርትና እርሻ ጠል ዜጐች ክፍት የሥራ ቦታ መሆኑ ያቆማል። ፖለቲካ የእፍረት የለሽ ብልጣብልጦች ቀኑን መስሎ በመኖር የተካኑ አድርባዮች አውድማ መሆኑ አክትሞ ልሂቃን የሚገርዙት፤ብዝኃኑ የሚያፀኑት የወይን እርሻ ይሆናል። የነቃ ህዝብ ከአገብዳጅነት የራቀ ስለሆነ መሪዎቹን ይዘውራል እንጂ አይዘውሩትም። ፍላጎቶቹን ፊት ለፊት ተነጋግሮ ይተባበራል ካልሆነም በሰላም መለያየት የሚባል አማራጫ እንዳለ ያውቃል። ያልቆጠራቸውን ጥቂቶች 'ጠርዘኞች' ብሎ በድንጋይ አይወግርም፤ሃሳብ ዳርቻ የሌለው አጽናፍ መሆኑን ቀልቡ ይነግረዋል። በዲሞክራሲያዊ አግባብ ከተከወነ እና የህዝብ ይሁንታ ካገኘ፤ ሀገረ-መንግስቱ ወደ ኮንፈደራልም ሆነ ፈድራል ቢያዘነብል ወይም ጭልጥ ብሎ አህዳዊ ቢሆን ውጤቱን የሚቀበል ፖለቲካዊ ብስለት ያለው ህዝብ በረጅም ጊዜ ሂደት ወደመፍጠር ከተጓዝን ሌላው ዕዳው ገብስ ነው።

አብይ አህመድ እያዳፋት 'ዙሪያዋ ገደል' ለሆነባት ሀገር ስለነገዋ ከዚህ በላይ እርግጠኛ በሆነ ፖለቲካዊ ቀለም መሳል በእጅጉ የሚፈለገውን ህብረት ስለሚጎዳ ጥንቃቄ ማድረጉ መልካም ነው። መሠረታዊ መግባቢያ (The bare minimum manifesto) እንዲቀይዱልን ሃላፊነት ለምንሰጣቸው ሽክም የሚሆን የፍላጎት ዝርዝር አናብዛ።

አንባቢ ሆይ!

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሶስቱ የጋራ የመሰረታዊ መግባቢያ አጀንዳዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

1. አውራ ወንጀለኞችን የማያካትት ሰላማዊ ሽግግር (አንዱ የሌላውን ፍርሃትና ስጋት ተረድቶ ያለስር-ነቀል ህገመንግስታዊ ለውጥ የሽግግር መንግስት መስረታ መንገዶች ላይ አቋም መያዝ)
2. ወደ እውነትን ማፈላላግና ዕርቅ ላይ ያጋደለ የሽግግር ፍትህ (የሆነው የሆነው ሚሊዮኖችን ባሳተፈ የጦር ወንጀል እንደመሆኑ አውራዎቹን መርጠን ካልሆነ ፍጹም ፍትህን ማስፈን ከባድ ነው፤ ስለዚህ የዚህ መሠረታዊ መግባቢያ ግብ እውነትን መፈለግ፤ እንዳይደገም ካለፈው መማር እና እርቅን እንዴት እናምጣ የሚለው ላይ ማተኮር)

3. የዲሞክራሲ ተቋማትን ግንባታና የዲሞክራሲያዊ ባህል አብዮት ማፋፋም (
   እዚህ ሥር የሚከተሉት ጥያቄዎችን የሚዳስስ ስራ እንደሚካተት ይጠበቃል፡፡
   የፀጥታ እና ጦር ሃይሉ ሳይፈርስ እንዴት ተመልሶ ይዋቀር? ፍርድቤቶች፣
   ምርጫ ቦርድ እና ሌሎችም ተቋማት እንዴት ተመልሰው ተዋቅረው
   የዴሞክራሲን ልምምድ ያግዙ? ያደሩ የህዝብና እና ቤት ቆጠራ ስራዎች
   እንዴት ተቀላጥፈው የፈፀሙ?)

በፖለቲካ እና ህዝብ አስተዳደር፣በህግመንግስታዊ ህግ፣ በዓለም-ዓቀፍ ግንኙነት፣በኢኮኖሚ በታሪክ እና ሌሎች ስነ-ሰብ የጥናት ዘርፍ ምሁራኖቻችን እና ሌሎች ሊሂቆቻችን ተሰብስባችሁ መሠረታዊ መግባቢያ (The bare minimum manifesto or BMM) ቅረፁ ስትባሉ አበል ትጠይቁ ይሆን? መተባባር ሳትችሉ ቀርታችሁ 'በገጠር እርሻ ጠል፣ በከተማም ትምህርት ጠል' ብለው አቶ ልደቱ ለገለፁት አጥፊ ስብስብ ሀገራችሁን ትተዋት ይሆን? ይህን ጥያቄ በአሰገምጋሚ አወንታ (resounding yes) ካልመለሳችሁ ገዢዎቻችን ጥፋት የለባቸውም፡፡

አስተያየት ካላችሁ ጸሃፊውን በ libaro123456@gmail.com ማግኘት ትችላላችሁ፡፡